የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

# ፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ

# FEDERAL NEGARIT GAZETA

OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA

አሥራአምስተኛ ዓመት ቁጥር ፴፫
አዲስ አበባ ግንቦት ፬ ቀን ፳፻፩ ዓ.ም

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

15th Year No.33
ADDIS ABABA 12th May, 2009

ማውጫ

አዋጅ ቁጥር ፮፻፳፮/፳፻፩ ዓ.ም

አነስተኛ የፋይናንስ ሥራ አዋጅ … ገጽ ፬ሺ፯፻፫

CONTENTS

Proclamation No. 626 /2009

Micro-Financing Business Proclamation Page ……. 4703

## አዋጅ ቁጥር ፮፻፳፮/፳፻፩

## አነስተኛ የፋይናንስ ሥራ አዋጅ

አነስተኛ የፋይናንስ ተቋማት በገጠር በግብርና እና በሌሎች መሰል ሥራዎች እንዲሁም በገጠርና በከተማ በጥቃቅንና አነስተኛ የሥራ መስኮች ለተሰማሩ ሰዎች የፋይናንስ አገልግሎት በመስጠት ረገድ ከፍተኛ ሚና ስለሚጫወቱ፣

የአነስተኛ የፋይናንስ ሥራ ዕድገትና ጤናማነት ይበልጥ እንዲጎለብት ተስማሚ የሆነ ሕጋዊ ማዕቀፍ እንዲኖር ማድረግ አስፈላጊ በመሆኑ፤

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ መንግሥት አንቀጽ ፶፭/፩/ መሠረት የሚከተለው ታውጇል።

## ክፍል አንድ
## ጠ ቅ ላ ላ

### ፩. አጭር ርዕስ

ይህ አዋጅ "አነስተኛ የፋይናንስ ሥራ አዋጅ ቁጥር ፮፻፳፮/፳፻፩" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል።

### ፪. ትርጓሜ

የቃሉ አግባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ አዋጅ ውስጥ፤

## PROCLAMATION NO. 626/2009

## MICRO FINANCING BUSINESS PROCLAMATION

**WHEREAS**, micro-financing institutions play an important role in providing access to financial services to rural farmers and people engaged in other similar activities as well as micro and small-scale rural and urban entrepreneurs;

**WHEREAS**, it is necessary to have an appropriate legal framework that further enhances the development and soundness of the micro-financing business;

**NOW, THEREFORE,** in accordance with Article 55(1) of the Constitution of the Federal Democratic Republic of Ethiopia, it is hereby proclaimed as follows:

## PART ONE
## GENERAL

### 1. Short Title

This Proclamation may be cited as the "Micro-Financing Business Proclamation No. 626/2009"

### 2. Definitions

In this Proclamation, unless the context requires otherwise:

፩/ "ፈቃድ የተሰጠው ተቋም" ማለት በብሔራዊ ባንክ አነስተኛ የፋይናንስ ሥራ እንዲሰራ ፈቃድ የተሰጠው ማናቸውም የፋይናንስ ተቋም ነው፤

፪/ "ዋና ሥራ አስፈፃሚ" ማለት በማናቸውም የማዕረግ ስም የሚጠራም ቢሆን የአንድን አነስተኛ የፋይናንስ ተቋም የዕለት ተዕለት ሥራዎች በዋና ኃላፊነት የመምራት ሥልጣን የተሰጠው ሰው ነው፤

፫/ "ኩባንያ" ማለት በኢትዮጵያ የንግድ ሕግ መሠረት የተሰጠውን ትርጓሜ የያዘ ሆኖ አክሲዮኖቹ በሙሉ በኢትዮጵያውያን ወይም በሙሉ በኢትዮጵያውያን ባለቤትነት በተቋቋሙ ድርጅቶች የተያዘ በኢትዮጵያ ሕግ መሠረት የተመዘገበና ዋና መሥሪያ ቤቱ በኢትዮጵያ የሆነ አክሲዮን ማኅበር ነው፤

፬/ "የግዴታ ቁጠባ" ማለት ገንዘቡን የሚቆጥቡት ግለሰቦችም ሆኑ ቡድኖች ፈቃድ ከተሰጠው ተቋም ብድር ለመውሰድ ብቁ ለመሆንና ለሚያገኙት ብድር በመያዣነት እንዲያገለግል በግዴታ የሚያስቀምጡት የቁጠባ ገንዘብ ነው፤

፭/ "ዳይሬክተር" ማለት በማናቸውም የማዕረግ ስም የሚጠራ ቢሆንም አነስተኛ የፋይናንስ ተቋም የዳይሬክተሮች ቦርድ አባል ነው፤

፮/ "የፋይናንስ ተቋም" ማለት መድን ሰጪ ኩባንያ፣ ባንክ፣ አነስተኛ የፋይናንስ ተቋም፣ የፖስታ ቁጠባ ድርጅት፣ የሐዋላ ድርጅት ወይም በብሔራዊ ባንክ የሚወሰን ሌላ ተመሳሳይ ድርጅት ነው፤

፯/ "የፋይናንስ ኪራይ" ማለት አከራዩ፤

ሀ/ ቀደም ሲል ይዞት የሚገኘውን የካፒታል ዕቃ፣ ወይም

ለ/ በተከራዩ መራጭነት አቅራቢ ተብሎ ከሚጠራው ሦስተኛ ወገን የሚገዛውን የካፒታል ዕቃ፤

ተከራዩ በተወሰነ ጊዜ ውስጥ ተከፍሎ የሚያልቅ በሁለቱ ወገኖች ስምምነት የተወሰነ ክፍያ በተወሰነ ጊዜ በመፈጸም እንዲጠቀምበት የሚያከራይበት፣ የኪራይ ስምምነቱ ጸንቶ በሚቆይበት ጊዜ ውስጥ አከራዩ በካፒታል ዕቃው ላይ ሙሉ የባለቤትነት መብት ይዞ የሚቆይበትና የኪራይ ዘመኑ ሲያበቃ ሁለቱም ወገኖች ከተስማሙ ተከራዩ የካፒታል ዕቃውን ሊገዛ የሚችልበት የኪራይ ዓይነት ነው፤

1/ "authorized institution" mean any financial institution licensed by National Bank to carry on micro-financing business;

2/ "chief executive officer" mean a person, by whatever title that person may be referred to, who is primarily responsible for the day-to-day management of the affairs of micro-financing institution;

3/ "company" mean a share company as defined under the Commercial Code of Ethiopia in which the capital is wholly owned by Ethiopian nationals or organizations wholly owned by Ethiopian nationals, and registered under the laws of, and having its head office in Ethiopia;

4/ "compulsory savings" mean mandatory deposits made for the purpose of enabling the individuals or groups making the savings to qualify to receive loans from an authorized institution and to serve as collateral against the loans so obtained;

5/ "director" mean any member of the board of directors of a micro-financing institution, by whatever title he may be referred to;

6/ "financial institution" mean insurance company, bank,micro-financing institution, postal savings, money transfer institution or such other similar institution as determined by the National Bank;

7/ "financial lease" mean a type of leasing by which a lessor provides a lessee against payment of mutually agreed installments over a specified period with the use of specified capital goods which is:

a) either already acquired by the lessor; or

b) purchased by the lessor from a third party, known as the supplier, chosen and specified by the lessee;

and under which the lessor shall retain full ownership right on the capital goods during the period of the lease agreement, and subject to agreement between the two parties, the lessee may have an option to purchase the capital good outright after the termination of the lease period at an agreed price;

፰/ "የሂሳብ ዓመት" ማለት እንደ አውሮፓውያን ዘመን አቆጣጠር ከጁላይ ፩ ቀን ጀምሮ በቀጣዩ ዓመት ጁን ፴ ቀን የሚያበቃ የአነስተኛ የፋይናንስ ተቋም የሂሣብ ዓመት ነው፣

፱/ "የቡድን ዋስትና" ማለት የቡድን ተበዳሪዎች ከመካከላቸው አንዳቸው ፈቃድ ከተሰጠው ተቋም የተበደረውን ያልከፈለ እንደሆነ ብድሩን መልሶ ለመክፈል በአንድነትና በተናጠል ኃላፊ የሚሆኑበት የዋስትና አሰራር ነው፣

፲/ "አነስተኛ የፋይናንስ ሥራ" ማለት ፈቃድ በተሰጠው ተቋም አማካይነት በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፫/፪/ ላይ የተዘረዘሩትን ሥራዎችና ሌሎች ተዛማጅነት ያላቸውን ተግባራትን የሚያጠቃልል የንግድ ሥራ ነው

፲፩/ "አነስተኛ የፋይናንስ ተቋም" ማለት በገጠርም ሆነ በከተማ በአነስተኛ የፋይናንስ ሥራና በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፫/፪/ በተጠቀሱት ሌሎች ሥራዎች ለመሰማራት በዚህ አዋጅ መሠረት ፈቃድ የተሰጠው ኩባንያ ነው፤

፲፪/ "ብሔራዊ ባንክ" ማለት የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ ነው፤

፲፫/ "ሰው" ማለት የተፈጥሮ ወይም በሕግ የሰውነት መብት የተሰጠው አካል ነው፤

፲፬/ "የችሎታ መመዘኛ" ማለት ብሔራዊ ባንክ በሚያወጣው መመሪያ የሚወሰን ተፈላጊ የትምህርት ደረጃ፣ የሥራ ልምድ፣ የብቃትና የሥነ-ምግባር መመዘኛ ነው፤

፲፭/ "ሞግዚት" ማለት ብሔራዊ ባንክ ወይም በብሔራዊ ባንክ የተሾመ ሰው ሲሆን ተግባሩም ችግር ያለበትን አነስተኛ የፋይናንስ ተቋም በመረከብ አሰራሩን እንደገና በማዋቀር ተቋሙን ጤናማ ማድረግ ወይም ማፍረስ ነው፤

፲፮/ "የውዴታ ቁጠባ" ማለት በባለሂሣቡ በማናቸውም ጊዜ በሙሉ ወይም በከፊል ሊወጣ የሚችል ፈቃድ በተሰጠው ተቋም ውስጥ ተቀማጭ የሆነ ገንዘብ ነው፤

፲፯/ "ከፍተኛ የሥራ ኃላፊ" ማለት የዋና ሥራ አስፈፃሚ ምክትል የሆነ ወይም ተጠሪነቱ በቀጥታ ለዳይሬክተሮች ቦርድ የሆነ ማንኛውም የአነስተኛ የፋይናንስ ተቋም የሥራ ኃላፊ ነው፣

፲፰/ ማንኛውም በወንድ ጾታ የተነገረው አገላለጽ ሴትንም ይጨምራል።

8/ "financial year" mean the financial year of a micro-financing institution running from July1st to June 30th of the following year;

9/ "group guarantee" mean a guarantee mechanism whereby a group of borrowers undertake to be liable jointly and severally for the repayment of a loan taken from an authorized institution in the event of default by any one of them;

10/ "micro-financing business" mean the provision of financial services as specified under Article 3(2) of this Proclamation by authorized institution;

11/ "micro-financing institution" mean a company licensed under this Proclamation to engage in micro-financiing business in rural and urban areas and other activities specified under Article 3(2) of this Proclamation;

12/ "National Bank" mean the National Bank of Ethiopia;

13/ "person" mean any natural or juridical person;

14/ "qualification of competency" mean required education, experience, fitness and propriety as prescribed by directives to be issued by the National Bank;

15/ "receiver" mean the National Bank or a person appointed by the National Bank to take control of a problem micro-financing institution for the purpose of restructuring its operations in order to make it sound or to terminate the existence of such institution;

16/ "voluntary savings" mean any deposit made with an authorized institution, which may be withdrawn partially or totally at any time by the account holder;

17/ "senior officer" mean any officer of a micro-finance institution who is deputy to the chief executive officer or is directly reporting to the board of directors.

18/ any expression in the masculine gender includes the feminine.

## ፫. አነስተኛ የፋይናንስ ተቋማት ዓላማና ተግባር

፩/ የአነስተኛ ፋይናንስ ተቋም ዋና ዓላማ ገንዘብ መሰብሰብና በገጠርና በከተማ በግብርና፣ በጥቃቅንና አነስተኛ የሥራ መስኮች እንዲሁም በሌሎች መሰል ሥራዎች ለተሰማሩ ሰዎች ጣሪያው በብሄራዊ ባንክ የሚወሰን ብድር መስጠት ይሆናል።

፪/ በዚህ አዋጅ የተደነገጉት ሁኔታዎች እንደተጠበቁ ሆነው፣ ማናቸውም አነስተኛ የፋይናንስ ተቋም የሚከተሉትን በሙሉ ወይም በከፊል ሊያከናውን ይችላል፡-

ሀ/ የውዴታም ሆነ የግዴታ ቁጠባ፣ በተጠየቀ ጊዜ የሚከፈል እንዲሁም የጊዜ ገደብ ተቀማጭ መቀበል፣

ለ/ በገጠር እና በከተማ በግብር እና በሌሎች ሥራዎች እንዲሁም በገጠርና በከተማ በጥቃቅንና አነስተኛ የሥራ መስኮች ለተሰማሩ ሰዎች ብድር መስጠት፤

ሐ/ በኢትዮጵያ ውስጥ የሚከፈሉ የሃዋላ ሰነዶችን ማውጣትና መቀበል፤

መ/ ብሔራዊ ባንክ በሚያወጣው መመሪያ መሠረት አነስተኛ የመድን ሥራ መሥራት፤

ሠ/ ዓላማቸው ገቢ ማስገኘት የሆነ እንደ ግምጃ ቤት ሰነዶችን እና ሌሎች የአጭር ጊዜ የንግድ ወረቀቶችን ብሔራዊ ባንክ በሚወስነው መሠረት መግዛት፤

ረ/ ሥራውን የሚያከናውንባቸውን ሕንፃዎች ጨምሮ ማናቸውንም የሚንቀሳቀስና የማይንቀሳቀስ ንብረት በባለቤትነት መያዝ መንከባከብና ለሌሎች ማስተላለፍ፤

ሰ/ በከተማና በገጠር በጥቃቅንና አነስተኛ የሥራ መስኮች የተሰማሩ ሰዎች የሚያካሂዱቸውን ገቢ የሚያስገኙ ፕሮጀክቶችን ማገዝ፤

ሸ/ ለደንበኞች የአመራር፣ የገበያ፣ የቴክኒክና አስተዳደራዊ ምክር መስጠትና በእነዚህም መስኮች አገልግሎቶች ለማግኘት እንዲችሉ ማገዝ፤

ቀ/ ለጥቃቅንና ለአነስተኛ የንግድ ሥራዎች ዓላማ የሚውል ገንዘብ ማስተዳደር፤

በ/ የሀገር ውስጥ ሐዋላ አገልግሎት መስጠት፤

## 3. Purpose and Activity of Micro-Financing Institutions

1/ The main purpose of a micro-financing institution shall be to collect deposits and extend credit to rural and urban farmers and people engaged in other similar activities as well as micro and small scale rural and urban entrepreneurs, the maximum amount of which may be determined by the National Bank.

2/ Subject to conditions set under this Proclamation, a micro-financing institution may engage in some or all of the following:

a) accepting both voluntary and compulsory savings as well as demand and time deposits;

b) extending credit to rural and urban farmers and people engaged in other similar activities as well as micro and small-scale rural and urban entrepreneurs;

c) drawing and accepting drafts payable within Ethiopia;

d) micro-insurance business as prescribed by directive to be issued by the National Bank;

e) purchasing income-generating financial instruments such as treasury bills and other short term instruments as the National Bank may determine as appropriate;

f) acquiring, maintaining and transferring any movable and immovable property including premises for carrying out its business;

g) supporting income generating projects of urban and rural micro and small scale operators;

h) rendering managerial, marketing, technical and administrative advice to customers and assisting them to obtain services in those fields;

i) managing funds for micro and small scale businesses;

j) providing local money transfer services;

ተ/ የፋይናንስ ኪራይ አገልግሎት በካፒታል ዕቃ ኪራይ ንግድ ሥራ አዋጅ ቁጥር ፩፻፫/፲፱፻፺ መሠረት ለአርሶ አደሮች እንዲሁም በገጠርና በከተማ በጥቃቅንና በአነስተኛ የሥራ መስኮች ለተሰማሩ ሰዎች መስጠት፤ እና

ቸ/ ብሔራዊ ባንክ በየጊዜው በሚያወጣቸው መመሪያዎች በሚወሰኑ ሌሎች ሥራዎች መሰማራት።

## ክፍል ሁለት
## ስለአነስተኛ የፋይናንስ ሥራ ፈቃድ

### ፬. ፈቃድ የማውጣት አስፈላጊነት

፩/ ማንኛውም ሰው ከብሔራዊ ባንክ ፈቃድ ካላገኘ በስተቀር፣ በአነስተኛ የፋይናንስ ሥራ ላይ መሰማራት አይችልም፤ ሆኖም አግባብ ባለው ሕግ ፈቃድ የተሰጣቸው ባንኮች የተለየ የሥራ ፈቃድ ሳያስፈልጋቸው በአነስተኛ የፋይናንስ ሥራ ላይ ሊሰማሩ ይችላሉ።

፪/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ /፩/ የተደነገገውን በመተላለፍ ማናቸውም ሰው ተቀማጭ ገንዘብ ለመቀበል በማስታወቂያ ወይም በማግባቢያ ዘዴ መጠቀሙን ወይም አነስተኛ የፋይናንስ ሥራ እያካሄደ መሆኑን ብሔራዊ ባንክ ለማመን ምክንያት ሲኖረው ይህንኑ ሁኔታ ለማጣራት ባንኩ በዚሁ ሰው ይዞታ ሥር የሚገኙትን የሂሳብ መዝገቦች፣ ቃለ ጉባኤ፣ ጥሬ ገንዘብ፣ የዋስትና ሰነዶች፣ የገንዘብ ማዘዣዎች እና ሌሎች ሰነዶች እንዲቀርቡለት ለማድረግና ለመመርመር ወይም ለማስመርመር ይችላል።

### ፭. የፈቃድ ቅድመ ሁኔታዎች

፩/ አነስተኛ የፋይናንስ ሥራ ፈቃድ ለማግኘት የሚከተሉት ቅድመ ሁኔታዎች መሟላት አለባቸው፡-

ሀ/ በሚገባ የተሞላ የፈቃድ መጠየቂያ ቅጽና ብሔራዊ ባንክ የሚጠይቃቸው ሌሎች አባሪ ሰነዶች መቅረብ አለባቸው፤

ለ/ ማመልከቻ በሚቀርብበት ጊዜ በብሔራዊ ባንክ የተወሰነው የሰነድ መመርመሪያ ክፍያ መከፈል አለበት፤

ሐ/ ተቋሙ በኩባንያ መልክ መቋቋምና የመመሥረቻ ጽሑፉና የመተዳደሪያ ደንቡ በሚመለከተው የመንግሥት አካል ከመመዝገቡ በፊት በብሔራዊ ባንክ መጽደቅ አለበት፤

k) providing financial leasing services to peasant farmers, micro and small-scale urban and rural entrepreneurs in accordance with the Capital Goods Leasing Business Proclamation No. 103/1998; and

l) engaging in other activities as specified by directives of the National Bank from time to time.

## PART TWO
## LICENSING MICRO-FINANCING BUSINESS

### 4. Requirement of Obtaining License

1/ It is prohibited to engage in micro-financing business without obtaining a license from the National Bank; provided however, that banks licensed under the appropriate law may engage in micro-financing business without a separate micro-financing business license.

2/ Where the National Bank has reason to believe that a person, in contravention of sub-article (1) of this Article, is advertising for or soliciting deposits of money or transacting micro—financing business, it may, in order to ascertain the situation, require that all books, munutes, accounts, cash, securities, records, vouchers and other documents which are in the possession or custody of such person be submitted to it and inspect or cause the inspection of the same.

### 5. Conditions of Licensing

1/ The following conditions shall be fulfilled to secure a micro-financing business license:

a) a duly completed application in the prescribed format and other accompanying documents as specified by the National Bank shall be submitted;

b) an investigation fee, as specified by the National Bank, shall be paid at the time of submitting the application;

c) the institution shall be formed as a company and its memorandum and articles of association shall be approved by the National Bank before registration with the appropriate government organ;

መ/ ተቋሙ ያወጣቸው አክሲዮኖች በሙሉ የተፈረሙ ሆነው ከእነዚህም ውስጥ ቢያንስ ሩቡ በጥሬ ገንዘብ የተከፈለ መሆን አለበት፤

ሠ/ በብሔራዊ ባንክ የተወሰነው ዝቅተኛ የተከፈለ ካፒታል በጥሬ ገንዘብ መከፈልና በምሥረታ ላይ ባለው አነስተኛ የፋይናንስ ተቋም ስም በዝግ የባንክ ሂሳብ ውስጥ መቀመጥ አለበት፤

ረ/ የተቋሙ ዳይሬክተሮችና ዋናው ሥራ አስፈጻሚ ብሔራዊ ባንክ ያወጣውን የችሎታ መመዘኛ የሚያሟሉና ሹመታቸው በብሔራዊ ባንክ የፀደቀ መሆን አለበት።

፪/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ /፩/ የተዘረዘሩት እንደተጠበቁ ሆነው፣ የአነስተኛ የፋይናንስ ሥራ ፈቃድ ተጨማሪ ግዴታዎችን ለመደንገግ ብሔራዊ ባንክ መመሪያ ሊያወጣ ይችላል።

## ፮. ፈቃድ ስለመስጠት

፩/ ብሔራዊ ባንክ በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፭ መሠረት መቅረብ ያለባቸው መረጃዎች ተሟልተው ከቀረቡበት ቀን ጀምሮ ባሉት ፷ ቀናት ውስጥ በአነስተኛ የፋይናንስ ሥራ ፈቃድ ማመልከቻው ላይ ውሳኔ ይሰጣል።

፪/ ፈቃዱ የሚሰጠው በብሔራዊ ባንክ የተወሰነው የፈቃድ ክፍያ ሲከፈል ይሆናል።

፫/ በዚህ አዋጅ መሠረት በብሔራዊ ባንክ የተሰጠ ፈቃድ አነስተኛ የፋይናንስ ሥራን ለማካሄድ የሚያስችል የመጨረሻው ፈቃድ ይሆናል።

፬/ ብሔራዊ ባንክ በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፭ ንዑስ አንቀጽ /፪/ መሠረት የፈቃድ ሁኔታዎችን ሲያሻሽል ማሻሻያው በሥራ ላይ እንዲውል ከታሰበበት ጊዜ ሰላሳ ቀን ቀደም ብሎ የሚመለከታቸው አነስተኛ የፋይናንስ ሥራ ተቋሞች እንዲያውቁት ይደረጋል።

፭/ ብሄራዊ ባንክ በሚያወጣው መመሪያ መሠረት አነስተኛ የፋይናንስ ተቋማት ቅርንጫፎችን መክፈት ይችላሉ።

## ፯. የፈቃድ ዕድሳት

ብሔራዊ ባንክ አነስተኛ የፋይናንስ ሥራ ፈቃድ የሚታደስበትን ሁኔታ በመመሪያ ሊወስን ይችላል።

d) all its issued shares shall be subscribed and, at a minimum, a quarter of the subscribed shares shall be fully paid in cash;

e) the minimum paid-up capital prescribed by the National Bank shall be paid in cash and deposited in a blocked account in a bank in the name of the prospective micro-financing institution;

f) the directors and the chief executive officer of the institution shall meet the qualification of competency prescribed by the National Bank and their appointment shall be approved by the National Bank.

2/ Without prejudice to the requirements specified under sub-article(1) of this Article, the National Bank may issue directives to presceibe additional conditions of licensing.

## 6. Issuance of License

1/ The National Bank shall decide on a micro-financing business license application within 60 days from the last date of receipt of all information to be submitted in accordance with Article 5 of this Proclamation.

2/ The license shall be issued upon pryment of the licensing fee prescribed by the National Bank.

3/ A license granted by the National Bank pursuant to this Proclamation shall constitute final authorization to carry on a micro-financing business.

4/ Where the National Bank amends the conditions of licensing in accordance with sub article (2) of Article 5 of this Proclamation, it shall notify the amendments to the concerned micro-financing institutions thirty days before the date on which the amendment becomes effective.

5/ In accordance with the directive to be issued by the National Bank, micro-financing institutions may open branches.

## 7. Renewal of License

The National Bank may issue directives on conditions of renewal of micro-financing business license.

## ፰. ፈቃድ ስለመሰረዝ

፩/ ብሔራዊ ባንክ የማንኛውንም አነስተኛ የፋይናንስ ተቋም የሥራ ፈቃድ በሚከተሉት ምክንያቶች ለመሰረዝ ይችላል፡-

ሀ/ ለተቋሙ ፈቃድ የተሰጠው በተሳሳተ ወይም በሀሰት መረጃ ላይ ተመስርቶ መሆኑ ሲረጋገጥ፣ ወይም

ለ/ ተቋሙ ፈቃድ በተሰጠው በ፲፪ ወራት ውስጥ ሥራ ሳይጀምር የቀረ እንደሆነ።

፪/ ብሔራዊ ባንክ የማናቸውንም አነስተኛ የፋይናንስ ተቋም ፈቃድ እንዲሰረዝ ሲወስን የተቋሙ ዋና መሥሪያ ቤት በሚገኝበት አካባቢ በሰፊው በሚሰራጭ ጋዜጣ ውሳኔውን አሳትሞ ያወጣል።

፫/ ፈቃድ የመሰረዝ ውሳኔ በጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ወይም ብሔራዊ ባንክ ከሚወስነው ማናቸውም ሌላ ቀን ጀምሮ ተፈጻሚ ይሆናል።

፬/ ፈቃዱ የተሰረዘበት አነስተኛ የፋይናንስ ተቋም የፈቃድ ስረዛው ውሳኔ ተፈጻሚ ከሆነበት ቀን ጀምሮ ማናቸውንም ዓይነት አነስተኛ የፋይናንስ ሥራ መሥራት አይችልም።

፭/ ብሔራዊ ባንክ ፈቃድ ለመሰረዝ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ /፩/ መሠረት በሰጠው ውሳኔ ቅር የተሰኘ ማንኛውም ሰው የፈቃድ ስረዛው ውሳኔ ተፈጻሚ ከሆነበት ቀን ጀምሮ በ፴ ቀናት ውስጥ ለፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ሊያመለክት ይችላል።

## ክፍል ሦስት
## የአሠራርና የፋይናንስ ግዴታዎችና ገደቦች

## ፱. አነስተኛ የፋይናንስ ሥራ ስለመጀመር

ፈቃድ የተሰጠው አነስተኛ የፋይናንስ ተቋም፣

፩/ ብሔራዊ ባንክ ባወጣው መመሪያ መሠረት ሥራ ከመጀመሩ በፊት ማሟላት የሚገባውን ሁኔታዎች ማሟላት፣ እና

፪/ ፈቃዱ ከተሰጠበት ቀን ጀምሮ ባሉት ፲፪ ወራት ውስጥ ሥራ መጀመር፣ አለበት።

## 8. Revocation of License

1/ The National Bank may revoke the license of a micro-financing institution where:

a) it is confirmed that the license was issued on the basis of false information; or

b) the institution has failed to commence operations within 12 months following the grant of the license.

2/ The decision to revoke the license of a micro-financing institution shall be published by the National Bank in a newspaper widely circulating at the place where the head office of the micro-financing institution is situated.

3/ Revocation of license of a micro-financing institution shall become effective on the date of its publication or on any other date as the National Bank may specify.

4/ Any micro-financing institution shall be prohibited from engaging in any micro-financing business starting from the effective date of the revocation of its license.

5/ Any person aggrieved by the decision of the National Bank to revoke the license of a micro-financing institution in accordance with sub-article (1) of this Article may petition to the Federal High Court within 30 days from the effective date of the revocation.

## PART THREE
## OPERATIONAL AND FINANCIAL REQUIREMENTS AND LIMITATIONS

## 9. Commencement of Operation

A micro-financing institution to which a license is granted shall;

1/ before commencing operation, fulfill requirements prescribed by directives issued by the National Bank, and

2/ commence its operation within 12 months from the date of issuance of the license.

## ፲. <u>አክስሲዮኖች የመያዝ ገደብና የአክሲዮን መዝገብ ስለመያዝ</u>

፩/ አንድ ባለአክሲዮን በማንኛውም አነስተኛ የፋይናንስ ተቋም ስለሚኖረው የአክሲዮን መጠን ብሔራዊ ባንክ መመሪያ ሊያወጣ ይችላል፡፡

፪/ ማናቸውም አነስተኛ የፋይናንስ ተቋም ብሔራዊ ባንክ በሚወስነው መሠረት የባለአክሲዮኖችን ስም ዝርዝርና ድምፅ የመስጠት መብታቸውን የሚያሳይ የአክሲዮን መዝገብ ይይዛል፡፡ በዚህም መዝገብ የተመዘገበ ማንኛውም የአክሲዮን ዝውውር የህግ ውጤት ይኖረዋል፡፡

፫/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ /፪/ የተመለከተው መዝገብ በአነስኛ የፋይናንስ ተቋሙ መደበኛ የሥራ ሰዓት ሕዝብ ያለክፍያ ማየት በሚችልበት ሁኔታ በተቋሙ ዋና መሥሪያ ቤት ይቀመጣል፡፡

## ፲፩. <u>አነስተኛ የፋይናንስ ተቋም አመራር ቦታ ስለሚይዙ ሰዎች</u>

፩/ የማናቸውም አነስተኛ የፋይናንስ ተቋም የዳይሬክተሮች ቦርድ አባላትና ዋና ሥራ አስፈፃሚ ብሔራዊ ባንክ ባወጣው መመሪያ የተወሰኑትን የችሎታ መመዘኛ መስፈርቶች ያሟሉ መሆኑና ሹመታቸውም በብሔራዊ ባንክ የፀደቀ መሆን አለበት፡፡

፪/ አንድ ሰው በአነስተኛ የፋይናንስ ተቋም ውስጥ በቦርድ አባልነት ቢበዛ ለስንት ዓመታት ማገልገል እንደሚችልና እንደገና የሚመረጥበትን ሁኔታ ብሔራዊ ባንክ በመመሪያ ሊወስን ይችላል፡፡

፫/ የሌላ የማናቸውም ሕግ ድንጋጌዎች እንደተጠበቁ ሆነው፣ የማናቸውም አነስተኛ የፋይናንስ ተቋም ዳይሬክተር፣ ዋና ሥራ አስፈፃሚ፣ ከፍተኛ የሥራ ኃላፊ ወይም በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ በኢትዮጵያ ውስጥ በአነስተኛ የፋይናንስ ተቋም ሥራ መሪነት የሚሳተፍ ሰው፤

ሀ/ በኢትዮጵያ ውስጥም ሆነ በውጪ ሀገር የመክሰር ውሳኔ የተሰጠበት ከሆነ፣ ወይም

ለ/ በኢትዮጵያ ውስጥም ሆነ ከኢትዮጵያ ውጪ እምነት በማጉደል ወይም በማጭበርበር ወንጀል የተፈረደበት ከሆነ፤

ራሱን ከአነስተኛ የፋይናንስ ተቋም አመራር ማግለል አለበት፡፡

## 10. <u>Acquisition of Shares and Maintaining Shares Register</u>

1/ The National Bank may issue directives on the amount of shares that may be held by a person in a micro-financing institution.

2/ Every micro-financing institution shall maintain a register, in such form as the National Bank may approve, which shall show the list of shareholders with voting rights. Any transfer of shares, which is recorded in the register, shall have legal effect.

3/ The register required to be maintained under sub-article (1) of this Article shall be kept open for inspection by members of the public, without charge, at the micro-financing institution's principal place of business during the micro-financing institution's normal working hours.

## 11. <u>Persons Assuming Management Positions of Micro-financing Institutions</u>

1/ The directors and the chief executive officer of a micro-financing institution shall meet the qualification of competency prescribed by the National Bank and their appointment shall be approved by the National Bank.

2/ The National Bank may determine by directives the maximum number of years a person may serve on the board of a micro-financiing institution and the conditions for his re-election.

3/ Without prejudice to the provisions of any other law, any person who is a director, chief executive officer, senior officer or is otherwise directly or indirectly concerned in the management of a micro-financing institution in Ethiopia, shall cease to exercise such function if:

a) declared bankrupt, whether in Ethiopia or elsewhere; or

b) convicted of an offence involving dishonesty or fraud, whether in Ethiopia or elsewhere.

፬/ ብሔራዊ ባንክ የአነስተኛ ፋይናንስ ተቋም ዳይሬክተሮች ቦርድን ተግባራት፣ ኃላፊነት፣ ግዴታዎችንና መልካም የኩባንያ ሥራ አመራርን በሚመለከት መመሪያ ሊያወጣ ይችላል፡፡

## ፲፪. የውጭ ኦዲተር ስለመሾም

፩/ ማናቸውም አነስተኛ የፋይናንስ ተቋም በብሔራዊ ባንክ ተቀባይነት ያለው የውጭ ኦዲተር መሾም አለበት፡፡ የውጭ ኦዲተር የሌለው ከሆነም ይህንኑ ወዲያውኑ ለብሔራዊ ባንክ ማሳወቅ አለበት፡፡

፪/ ማናቸውም አነስተኛ የፋይናንስ ተቋም በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ /፩/ መሠረት የውጭ ኦዲተር ያልሾመ እንደሆነ እስከሚቀጥለው የተቋሙ ዓመታዊ የባለአክሲዮኖች ጠቅላላ ስብሰባ ድረስ የሚያገለግል የውጭ ኦዲተር ብሔራዊ ባንክ ይሾምለታል፡፡ ለተሾመው ኦዲተር የሚደረገው የአገልግሎት ክፍያም በተቋሙ ይሸፈናል፡፡

፫/ በማናቸውም አነስተኛ የፋይናንስ ተቋማት ኦዲት ሥራ ለማካሄድ የሚሾሙ የውጭ ኦዲተሮች፤

ሀ/ ማሟላት ስለሚገባቸው ዝቅተኛ የችሎታ መመዘኛ መስፈርት፣

ለ/ የምርመራ ይዘትና ጥልቀት፣ እና

ሐ/ የኦዲተሮች የሹመት ዘመን፣

በተመለከተ ብሔራዊ ባንክ በየጊዜው መመሪያዎችን ሊያወጣ ይችላል፡፡

፬/ የሚከተሉት ሰዎች የማናቸውም አነስተኛ የፋይናንስ ተቋም የውጭ ኦዲተር ሆነው መሾም አይችሉም፤

ሀ/ የአነስተኛ የፋይናንስ ተቋሙ ባለአክሲዮን፣ ዳይሬክተር፣ ዋና ሥራ አስፈፃሚ ወይም ሠራተኛ፤

ለ/ በዚህ ንዑስ አንቀጽ ተራ ፊደል /ሀ/ የተመለከተ ሰው የትዳር ጓደኛ ወይም አንደኛ ደረጃ የሥጋ ወይም የጋብቻ ዘመድ፤

ሐ/ በዚህ ንዑስ አንቀጽ ተራ ፊደል /ሀ/ ወይም /ለ/ የተመለከተ ሰው ሠራተኛ ወይም ሽሪክ የሆነበት የኦዲት ተቋም፡፡



4/ The National Bank may issue directive on duties, responsibilities and good corporate governance of the boards of directors of micro-financing institutions.

## 12. Appointment of External Auditors

1/ Every micro-financing institution shall appoint an external auditor satisfactory to the National Bank. Where it is without an external auditor it shall forthwith notify such fact to the National Bank.

2/ If a micro-financing institution fails to appoint an external auditor in accordance with the sub article (1) of this Articlle, the National Bank may appoint an auditor who shall serve until the next annual general meeting of shareholders of the institution. The remuneration of such auditor shall be paid by the institution.

3/ The National Bank may issue directives, from time to time, on;

a) the mimimum qualification required of external auditors appointed to perform audits of micro-financiing institutions;

b) the scope and depth of the audit; and

c) tenure of auditors.

4/ Any of the following persons may not be qualified for appointment as an external auditor of a micro-financing institution:

a) a shareholder, director, chief executive officer or employee of the institution;

b) a person who is a spouse or related by consanguinity or affinity to the first degree to a person referred to in paragraph (a) of this sub-article; or

c) a firm of auditors of which any of its partners or employees falls within the categories of persons described under paragraph (a) or (b) of this sub- article.

## ፲፫. የውጭ ኦዲተር ተግባሮችና ሪፖርቶች

፩/ አነስተኛ የፋይናንስ ተቋም የውጭ ኦዲተር ተግባር ተቀባይነት ባላቸው የኦዲት ደረጃዎች መሠረት የተቋሙን ሂሳብ መርምሮ ያገኛቸውን ውጤቶችና የደረሰባቸውን ድምዳሜዎች ለተቋሙ ባለ አክሲዮኖች እና ለብሔራዊ ባንክ ሪፖርት ማቅረብ ነው። በተጨማሪም የውጭ ኦዲተር ዝርዝር ግኝቶቹን ለብሔራዊ ባንክ በቀጥታ መላክ አለበት።

፪/ ብሔራዊ ባንክ የቀረበውን የኦዲት ሪፖርት ካላመነበት ድጋሚ የሂሣብ ምርመራ እንዲካሄድ ማዘዝ ወይም ሌላ የውጭ ኦዲተር በመሾም ሂሣቡ እንደገና እንዲመረመር ማድረግ ይችላል። በብሔራዊ ባንክ አዲስ ለተሾመው የውጭ ኦዲተር የሚደረገው ክፍያ በአነስተኛ የፋይናንስ ተቋሙ የሚሸፈን ይሆናል።

፫/ የማንኛውም አነስተኛ የፋይናንስ ተቋም የውጭ ኦዲተር የሂሣብ ምርመራ ተግባሩን በሚያካሂድበት ጊዜ፤

ሀ/ የዚህ አዋጅ ወይም የሌሎች አግባብ ያላቸው ሕጎች ድንጋጌዎች ወይም በዚህ አዋጅ መሠረት የወጡ ደንቦች ወይም መመሪያዎች በከፍተኛ ደረጃ መጣሳቸውን ወይም ያለመከበራቸውን፣

ለ/ በአነስተኛ የፋይናንስ ተቋሙ ወይም በማናቸውም የተቋሙ ዳይሬክተር ወይም ሠራተኛ የማጭበርበር ወይም ሌላ የእምነት ማጉደል ወንጀል መፈጸሙን፣

ሐ/ አነስተኛ የፋይናንስ ተቋሙ ካፒታል ፳፭ በመቶ ወይም ከዚያ በላይ በሆነ መጠን የሚቀንስ ኪሣራ የደረሰ መሆኑን፤

መ/ የአስቀማጮችን ወይም የገንዘብ ጠያቂዎችን ጥቅም አደጋ ላይ የሚጥል ከመደበኛው ወይም ከተለመደው አሠራር ውጭ ከባድ የሆነ የአሠራር ችግር መከሰቱን፣ ወይም

ሠ/ የገንዘብ አስቀማጮችን ወይም የገንዘብ ጠያቂዎችን የገንዘብ ጥያቄዎች በተቋሙ ንብረቶች ሊሸፈኑ መቻላቸውን ማረጋገጥ አለመቻሉን፣

ሲደርስበት ጉዳዩን ለብሔራዊ ባንክና ለሚመለከታቸው ሌሎች አካላት ወዲያውኑ ማሳወቅ አለበት።

## 13. Duties and Reports of External Auditors

1/ The duty of an external auditor of a micro-financing institution shall be to report his audit findings and conclusions, carried out on the basis of accepted auditing standards, to the shareholders of the institution and the National Bank. The external auditor shall also be required to submit the management letter to the National Bank.

2/ The National Bank may, if not satisfied with the audit report, commission a second audit or require the prompt appointment of a new auditor who shall make an independent report and whose remuneration shall be paid by the micro-financing institution.

3/ Where the external auditor of any micro-financing institution, in the course of the performance of his audit duties, finds out that:

a) there has been a serious breach of, or non-compliance with, the provisions of this Proclamation, other relevant laws or regulations or directives issued hereunder;

b) a criminal offence involving fraud or other dishonesty has been committed by the micro-financing institution or any of is directors or employees;

c) losses have been incurred which reduce the total capital of the micro-financing institution by 25% or more;

d) serious irregularities have occurred which may jeopardize the secutiry of its depositors or creditors;or

e) it is not possible to confirm that the claims of depositors and creditors of the micro-financing institution are capable of being met out of the assets of the micro-financing institution;

he shall immediately report the matter to the National Bank and other concerned bodies.

፬/ በማናቸውም አነስተኛ የፋይናንስ ተቋም የውጭ ኦዲተር ሆኖ የተሾመ ሰው በመደበኛ የሥራ ሂደትና ለሌላ ለማንኛውም ሰው ከሚሰጠው አገልግሎት ባልተለየ ሁኔታ ካልሆነ በስተቀር፣ በዚያው ተቋም ሂሣብ መያዝ ወይም ከተቋሙ ማንኛውንም ዓይነት አገልግሎት ማግኘት አይችልም፡፡

፭/ ብሔራዊ ባንክ የማናቸውም አነስተኛ የፋይናንስ ተቋም የሂሣብ ዓመት ከተጠናቀቀ በኋላ በምን ያህል ጊዜ የኦዲት ሪፖርት መውጣት እንዳለበት በመመሪያ ይወስናል፡፡

## ፲፬. የፋይናንስ ግዴታዎች

፩/ አነስተኛ የፋይናንስ ተቋም ሊኖረው የሚገባው ዝቅተኛ የተከፈለ ካፒታል መጠን ብሔራዊ ባንክ በሚያወጣው መመሪያ ይወሰናል፡፡

፪/ ብሔራዊ ባንክ የሚከተሉትን በሚመለከት መመሪያ ሊያወጣ ይችላል፦

ሀ/ አነስተኛ የፋይናንስ ተቋም ለማንኛውም ግለሰብ ወይም ቡድን ሊሰጥ ስለሚችለው ከፍተኛ የብድር መጠንና ችግር ላለባቸው ብድሮች ስለሚይዘው የመጠባበቂያ ሂሣብ፤

ለ/ በሥራ ላይ ያለ አነስተኛ የፋይናንስ ተቋም ሊኖረው ስለሚገባው የካፒታል መጠንና ገንዘብ-አከል ሀብቶች፤

ሐ/ አንድ አነስተኛ የፋይናንስ ተቋም ፈቃድ ከተሰጠበት ጊዜ ጀምሮ ቢዘገይ በስንት ዓመታት ውስጥ አትራፊ መሆን እንዳለበትና ከዚሁ ጋር ስለተያያዙ ጉዳዮች፤

መ/ ስለአነስተኛ የፋይናንስ ተቋም የፋይናንስ አፈፃፀም ደረጃ፤ እና

ሠ/ ስለአነስተኛ የፋይናንስ ተቋም ሂሣብ አያያዝ፣ የሥራ አመራር መረጃ ፍሰት፣ የውስጥ ቁጥጥርና በየጊዜው መቅረብ ስላለባቸው ሪፖርቶች፡፡

፫/ ብሔራዊ ባንክ አነስተኛ የፋይናንስ ተቋማት ለአደጋ የተጋለጡበትን ሁኔታ ግምት ውስጥ በማስገባት የተለያዩ የካፒታልና ገንዘብ-አከል ንብረቶች ግዴታዎችን ለተለያዩ አነስተኛ የፋይናንስ ተቋማት ሊያስቀምጥ ይችላል፡፡

4/ A person appointed as an external auditor of a micro-financing institution shall not operate an account with, or be granted any type of facility from, that institution except in the normal course of business and at an arms's length basis.

5/ The National Bank shall determine by directives the time limit for issuance of audit reports after the end of a micro-financing institution's financial year.

## 14. Financial Requirements

1/ The minimum paid up capital required to be maintained by a micro-financing institution shall be determined by directives to be issued by the National Bank.

2/ The National Bank may issue directives governing:

a) limits on the maximum credit to be extended by a micro-financing institution to any individual or group and provisioning for problem loans;

b) capital adequacy and liquidity levels to be maintained by a micro-financing institution in operation;

c) the maximum number of years after licensing within which a micro-financing institution shall be profitable and related matters;

d) financial performance standards of a micro-financing institution; and

e) keeping of books of accounts, management information system, internal control system and periodic reporting of a micro-financing institution.

3/ The National Bank may prescribe a different capital and liquidity requirements to be maintained by different micro-financing institutions depending on their risk profile.

## ፲፭. ስለፋይናንስ መዝገቦችና መረጃዎች ስለመስጠት

፩/ ማናቸውም አነስተኛ የፋይናንስ ተቋም:-

ሀ/ የሂሣብ መግለጫዎቹን ተቀባይነት ባላቸው የፋይናንስ ሪፖርት አዘገጃጀት ደረጃዎች መሠረት ማዘጋጀት፣

ለ/ የተቋሙን ሁኔታ በግልጽና በትክክል የሚያሳይ፣ የተቋሙን ሥራና የገንዘብ አቋሙን የሚያስረዳ እና ተቋሙ በዚህ አዋጅ ድንጋጌዎች እንዲሁም ብሔራዊ ባንክ ባወጣቸው መመሪያዎች መሠረት ሥራውን እያካሄደ ስለመሆኑ ብሔራዊ ባንክ ማረጋገጥ በሚችልበት ሁኔታ መዝገቦቹን መያዝ፤ እና

ሐ/ ብሔራዊ ባንክ በሚያወጣው መመሪያ እያንዳንዱን የሥራ እንቅስቃሴ ዓይነት የሚመዘግብበት የተለየ መዝገብና ሰነዶች መያዝ፣

አለበት።

፪/ ማናቸውም አነስተኛ የፋይናንስ ተቋም:-

ሀ/ ብሔራዊ ባንክ በሚወስነው የጊዜ ገደብ ውስጥ በሚገባ የተፈረሙ የፋይናንስ መግለጫዎችንና ሌሎች በብሔራዊ ባንክ የሚወሰኑ ሪፖርቶችን ለባንኩ ማቅረብ፣ እና

ለ/ በውጭ ኦዲተር የተመረመረ የሂሣብ ሚዛንና የትርፍና ኪሣራ መግለጫዎችን በሁሉም የተቋሙ ቅርንጫፎች ግልፅ በሆነ ቦታ ዓመቱን ሙሉ እንዲታዩ ማድረግ፣

አለበት።

፫/ ማናቸውም አነስተኛ የፋይናንስ ተቋም:-

ሀ/ ለገንዘብ አስቀማጮቹና ለሌሎች አበዳሪዎች ያለበትን ግዴታ ማሟላት እንደማይችል፣ ወይም

ለ/ ለገንዘብ አስቀማጮችና ለሌሎች አበዳሪዎች ክፍያዎችን በወቅቱ ለመፈፀም እንደሚሳነው፣

ሲገመት ሙሉውንና ትክክለኛውን ሁኔታ ለብሔራዊ ባንክ ማሳወቅ አለበት፤ በተጨ ማሪም ብሔራዊ ባንክ የሚጠይቃቸውን ሌሎች ሰነዶች ማቅረብ አለበት

## 15. Financial Records and Disclosure of Information

1/ Any micro-financiing institution shall:

a) prepare its financial statements in accordance with acceptable accounting standards;

b) keep such records as are necessary to exhibit clearly and correctly the state of its affairs and to explain its transactions and financial position and to enable the National Bank to determine whether the micro-financing institution had complied with the provisions of this Proclamation and directives issued by the National Bank; and

c) register and keep documents for each type of transaction in accordance with directives of the National Bank.

2/ Any micro-financing institution shall:

a) within a time period to be determined by the National Bank, submit to the National Bank duly signed financial statements and other reports as prescribed by it; and

b) exhibit at all branches, in a conspicuous place throughout the year, a copy of the last audited balance sheet and profit and loss statement.

3/ Any micro-financing institution shall, where it appears likely that:

a) it cannot meet its obligations to its depositors or other creditors; or

b) it may have to suspend payments to depositors or other creditors;

forthwith notify the National Bank of the full facts of the situation and also provide such other information as the National Bank may request.

፬/ ብሔራዊ ባንክ አግባብ አላቸው ብሎ የሚያምንባቸውን መረጃዎች ከአነስተኛ የፋይናንስ ተቋም መጠየቅና ማግኘት ይችላል፣ ሆኖም፣

ሀ/ የዚህ አዋጅ ድንጋጌዎችን ለማስፈጸም ሲባል፣

ለ/ የተቋሙን የፋይናንስ ጤናማነት ለማረጋገጥ፣

ሐ/ በሕግ ለተፈቀደላቸው ሰዎች፣

መ/ ብሔራዊ ባንኩ ተጠሪ ለሆነለት አካል፣

ሠ/ በፍርድ ቤት በመታዘዙ፣ ወይም

ረ/ ኢትዮጵያ የገባችባቸውን ዓለም አቀፍ ግዴታዎች ለመወጣት ሲባል፣ ካልሆነ በቀር እነዚህ መረጃዎች ለማንኛውም ሰው ተላልፈው አይሰጡም።

## ፲፮. የብድር አገልግሎት አሰጣጥ

ፈቃድ የተሰጠው ተቋም ለቡድኖችም ሆነ ለግለሰቦች ብድር መስጠት ይችላል። ተቋሙ እንደ አግባብነቱ በራሱ ውሳኔ ያለመያዣ፣ በመያዣ፣ በንብረት ወይም በቡድን ወይም በግለሰብ ዋስትና ብድር መስጠት ይችላል።

## ፲፯. ክልከላ

ከብሔራዊ ባንክ የጽሁፍ ፈቃድ ካላገኘ በስተቀር ማናቸውም አነስተኛ የፋይናንስ ተቋም የሚከተሉትን መፈጸም አይችልም፤

፩/ የተቋሙን ሥራ ወይም ተቋሙን ከሌላ ለማቀላቀል ወይም ለመሸጥ ማንኛውንም ውል መዋዋል፤

፪/ በመደበኛ የሥራ አፈፃፀም ተግባሩ ካልሆነ በቀር ንብረቱን በሙሉም ሆነ በከፊል ለሌላ ሰው ማስተላለፍ ወይም በሌላ መንገድ ማዛወር፤

፫/ በኪሣራ ምክንያት ካልሆነ በስተቀር የተቋሙን ካፒታል መቀነስ፤

፬/ የመመሥረቻ ጽሑፉን እና የመተዳደሪያ ደንቡን ማሻሻል ወይም ፈቃድ ያገኘበትን ስም መለወጥ፤

4/ The National Bank may collect any information from a micro-financing institution, as it may deem appropriate; provided, however, that such information may not be disclosed to any person unless the disclosure:

a) is made for the purpose of fulfilling the requirements of this Proclamation;

b) is required to ensure the financial soundness of the institution;

c) is made to recipients who are legally authorized to obtain such information;

d) is made to the body to which the National Bank is accountable;

e) is ordered by a court; or

f) is required for the purpose of meeting obligations which Ethiopia entered into under international agreement.

## 16. Extending of Loans

An authorized institution may extend loans to groups and to individuals. Loans may be made without collateral, secured by collateral or secured by group or individual guarantees as appropriate and at the discretion of the institution.

## 17. Prohibitions

Without the prior written approval of the National Bank, no micro-financing institution shall:

1/ enter into an agreement for the amalgamation or disposal of its business;

2/ transfer or otherwise dispose of the whole or any part of its property other than in the ordinary course of business;

3/ effect reduction of its capital, other than as a result of losses;

4/ amend its memorandum and articles of association or alter the name under which it is licensed;

፭/ ከተፈቀደለት አካባቢ ውጭ መሥራት፡፡

## ፲፰. በአነስተኛ የፋይናንስ ተቋም ላይ ስለሚደረግ ቁጥጥርና የማስተካከያ እርምጃዎች

፩/ ብሔራዊ ባንክ በየጊዜው ወይም በማናቸውም ጊዜ ያለቅድሚያ ማስጠንቀቂያ በማናቸውም አነስተኛ የፋይናንስ ተቋም ላይ በቦታው ተገኝቶ ቁጥጥር ማካሄድ ወይም እንዲካሄድ ማድረግ ይችላል፡፡

፪/ ከጠቅላላው ገንዘብ አስቀማጮች በቁጥር አንድ አስረኛ ወይም በአነስተኛ የፋይናንስ ተቋሙ ዘንድ ካለው ጠቅላላ ገንዘብ ውስጥ አንድ ስድስተኛ አስቀማጭ የሆኑ አመልካቾች በተቋሙ ላይ ምርመራ ማካሄድ አስፈላጊ መሆኑን የሚያስረዳ መረጃ አያይዘው ጥያቄ ካቀረቡ፣ ብሔራዊ ባንክ ማመልከቻ የቀረበበት ተቋም በጤናማ ሁኔታ መገኘቱንና የዚህ አዋጅ ድንጋጌዎች እንዲሁም በዚህ አዋጅ መሠረት የወጡ ደንቦችና መመሪያዎች የተቋሙን የሥራ እንቅስቃሴ በመምራት ሂደት ውስጥ መከበራቸውን ለማረጋገጥ በሚስጥር ምርመራ ማካሄድ ወይም እንዲካሄድ ለማድረግ ይችላል፡፡

፫/ አነስተኛ የፋይናንስ ተቋማትን የመቆጣጠሩ ተግባር በብሔራዊ ባንክ አንድ ባለሙያ ወይም ከአንድ በላይ በሆኑ ባለሙያዎች ወይም በሌሎች እምነት በሚጣልባቸውና ለዚህ ጉዳይ በብሔራዊ ባንክ በተቀጠሩ ባለሙያዎች ወይም ድርጅቶች ሊካሄድ ይችላል፡፡

፬/ አነስተኛ የፋይናንስ ተቋምን እንዲቆጣጠሩ በብሔራዊ ባንክ ሥልጣን የተሰጣቸው ሰዎች ወይም ድርጅቶች ቁጥጥር ከሚደረግበት አነስተኛ የፋይናንስ ተቋም ሠራተኞች የቁጥጥሩን ተግባር ውጤታማ በሆነ መንገድ ለማካሄድ አስፈላጊ የሆኑ መረጃዎችንና ስለ ተቋሙ ሁኔታ የሚገልፁ መዛግብትና የሥራ እንቅስቃሴ ማብራሪያዎች ለመጠየቅ ሥልጣን አላቸው፡፡

፭/ የቁጥጥር ሪፖርት ለሚመለከተው ተመርማሪ አነስተኛ የፋይናንስ ተቋም እንዲደርሰው ይደረጋል፡፡ በቀረበው ሪፖርት ላይ የመጨረሻ ውሳኔ ከመሰጠቱ በፊት ተመርማሪው ተቋም በሪፖርቱ ላይ አስተያየቱን እንዲያቀርብ ዕድል ይሰጠዋል፡፡

፮/ ለብሔራዊ ባንክ የቀረበው የቁጥጥር ሪፖርት ይዘት፡-

5/ operate outside the area for which it has been issued with a license.

## 18. Inspection of Micro-Financing Institution and Corrective Measures

1/ The National Bank may, periodically or at any time, without prior notice, make, or cause to be made, an on-site inspection on any micro-financing institution carrying on micro-finance business in Ethiopia.

2/ Where an application, accompanied with supporting evidence, is made to the National Bank by one-tenth of the total number of depositors or by any number of depositors holding not less than one-sixth of the deposits of a micro-financing institution, the National Bank shall examine, or cause to be examined, under conditions of secrecy, the affairs of the micro-financing institution in order to determine whether it is in a sound condition and the provisions of this Proclamation and regulations and directives issued hereunder have been compled with.

3/ Inspection of micro-financing institutions may be carried out by one or more officers of the National Bank or by trustworthy and qualified persons or firms employed by the National Bank for this purpose.

4/ Persons charged by the National Bank with inspection of a micro-financing institution shall be authorized to request from the personnel of the micro-financing institution such information or explanation of the records or transactions of the micro-financing institution that are necessay for the effective carrying out of the inspection.

5/ The inspection report shall be communicated to the examined micro-financing institution and, before the report is made final, it shall be given an opportunity to express its views on the report.

6/ The content of the inspection report submitted to the National Bank shall be considered as confidential by:

ሀ/ ቁጥጥሩን ባካሄዱት ሰዎች እንዲሁም ቁጥጥሩ በተደረገበት አነስተኛ የፋይናንስ ተቋም ዳይሬክተሮችና ሠራተኞች፣ እና

ለ/ የዚህን አዋጅ ድንጋጌዎችን ለማስፈጸም ወይም የሕዝብን ጥቅም ለማስከበር ሲባል ካልሆነ በቀር በብሔራዊ ባንክ፣ በምስጢር መጠበቅ አለበት፡፡

፯/ በተደረገው ቁጥጥር ተመርማሪው አነስተኛ የፋይናንስ ተቋም በኢትዮጵያ ፀንተው የሚገኙትን ሕጎች፣ ደንቦች ወይም መመሪያዎች ያልተከተለ መሆኑ ወይም አነስተኛ የፋይናንስ ሥራ እንዲሠራ በተሰጠው የሥራ ፈቃድ የተመለከቱትን ግዴታዎች ያልፈፀመ መሆኑ የተረጋገጠ እንደሆነ ወይም በማናቸውም አኳኋን የገንዘብ አስቀማጮችን ወይም የሕዝብን ጥቅም በሚጎዳ በማናቸውም ተግባር ላይ የተሰማራ እንደሆነ ወይም በሥራ አመራሩ ላይ ከባድ ድክመት የተከሰተ እንደሆነ ብሔራዊ ባንክ፦

ሀ/ አነስተኛ የፋይናንስ ተቋሙን ማናቸውም ተግባር በተመለከተ ለመነጋገር የባለአክሲዮኖች ወይም የዲሬክተሮች ቦርድ ስብሰባ እንዲጠራ ወይም የዚህ ተቋም ኃላፊዎች ምርመራውን በተመለከተ የብሔራዊ ባንክ ኃላፊዎችን እንዲያነጋግሩ ለማዘዝ፣

ለ/ አንድ ወይም ከዚያ በላይ ኃላፊዎቹን በተመርማሪው አነስተኛ የፋይናንስ ተቋም የዲሬክተሮች ቦርድ ወይም በእርሱ በተሰየመ በማናቸውም ኮሚቴ ወይም ሌላ አካል ስብሰባ ላይ እንዲገኙ ለመወከልና የተወካዮቹ አስተያየትም በተጠየቀሱት ስብሰባዎች ላይ እንዲሰማ ለማዘዝ፤

ሐ/ አነስተኛ የፋይናንስ ተቋሙ ሊወሰድ የሚገባውን የማስተካከያ እርምጃ እንዲወስዳ በጽሑፍ ለማዘዝ፣

መ/ በሚያወጣው መመሪያ መሠረት በአነስተኛ የፋይናንስ ተቋሙ አንድ ወይም ከዚያ በላይ በሆኑ ዳይሬክተሮች፣ ዋና ሥራ አስፈጻሚ እና ሌሎች ከፍተኛ የሥራ ኃላፊዎች ላይ የገንዘብ መቀጫ ለመወሰን ወይም ከሥራ እንዲታገዱ ወይም እንዲሰናበቱ ለማዘዝ፣

a) the persons carrying out the inspection, and the directors and employees of the inspected micro-financing institutions; and

b) the National Bank, unless it is for the purpose of fulfilling the requirements of this Proclamation or to the interest of the public;

7/ Where an inspection of a micro-financing institution results in a finding that the institution has failed to comply with applicable laws and directives or with the terms and conditions of license or has engaged in practices detrimental to the interests of depositors or has serious weaknesses in its corporate governance, the National Bank may:

a) require the inspected micro-financing institution to call a meeting of its shareholders or board of directors for the purpose of considering any matter arising out of, or relating to, the inspection or require the officers of such micro- financing institution to discuss any such matter with the officers of the National Bank;

b) depute one or more of its officers to watch the proceedings at any meeting of the board of directors of the inspected micro-financing institution or of any committee or of any other body constituted by it and require the inspected micro-financing institution to give an opportunity to the officers so deputed to be heard at such meetings;

c) instruct in writing corrective actions to be taken by the inspected micro-financing institution;

d) impose a fine, as prescribed by its directives, on the inspected micro-financing institution's one or more directors, the chief executive officer and other senior officers, or order their suspension or dismissal from duty;

ሠ/ አነስተኛ የፋይናንስ ተቋሙ አዲስ ቅርንጫፎችን እንዳይከፍት ለመከልከል፣

ረ/ የተቋሙን የአክሲዮን ትርፍ ድርሻ ክፍፍል ለመገደብ፣ ለማዘግየት ወይም ለመከልከል፣

ሰ/ አነስተኛ የፋይናንስ ተቋሙን ለተወሰነ ጊዜ በከፊልም ሆነ በሙሉ አነስተኛ የፋይናንስ ሥራ እንዳይሰራ ለማዘዝ፣ ወይም

ሸ/ አነስተኛ የፋይናንስ ተቋሙን ፈቃድ ለመሰረዝና ተቋሙን የማፍረስ ሂደት እንዲጀመር ለማድረግ፣

ይችላል፡፡

## ፲፱. ስለሞግዚት አስተዳደርና መፍረስ

፩/ ብሔራዊ ባንክ ከሚከተሉት አንዱ ወይም ከዚያ በላይ የሆኑ ሁኔታዎች በአንድ አነስተኛ የፋይናንስ ተቋም መኖራቸውን ሲያምን ተቋሙን ተረክቦ የሚቆጣጠር ሞግዚት ሊሾም ወይም ራሱ እንደሞግዚት ሆኖ ሊያገለግል ይችላል፡-

ሀ/ በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፰ ንዑስ አንቀጽ ፩/ሀ/ መሠረት የባንኩ ፍቃድ የተሰረዘ ከሆነ፤

ለ/ የአነስተኛ ፋይናንስ ተቋሙ ሀብት ለአስቀማጮችና ለሌሎች ገንዘብ ጠያቂዎች ከገባቸው ግዴታዎች ያነሰ ከሆነ፤

ሐ/ ሕግን ወይም መመሪያን በመተላለፍ ወይም ጥንቃቄ በጎደለው አሰራር ምክንያት በቀላሉ የማይገመት የሀብትና የገቢ ብክነት የተከሰተ ከሆነ፤

መ/ አነስተኛ የፋይናንስ ተቋሙ ሥራውን የሚያካሂደው ጤናማ ባልሆነ እና ጥንቃቄ በጎደለው ሁኔታ ከሆነ፤

ሠ/ በብሔራዊ ባንክ የተጣለ ማንኛውም ገደብ ሆን ተብሎ የተጣሰ ከሆነ፤

ረ/ ተቋሙ የሂሣብ መዝገቦችን፣ ሰነዶችን፣ ሬኮርዶችን ወይም ንብረቶችን የደበቀ ወይም ለቁጥጥር ተግባር ሥልጣን ለተሰጠው የብሔራዊ ባንክ ሠራተኛ ወይም ወኪል ያላቀረበ ከሆነ፤

e) prohibit the micro-financing institution from opening new branches;

f) restrict, suspend or prohibit payment of dividends;

g) direct the inspected micro-financing institution to temporarily suspend any one or all of its micro-financing business; or

h) revoke the license of the micro-financing institution and initiate the process of its liquidation.

## 19. Receivership and Liquidation

1/ The National Bank may appoint a receiver or itself act as a receiver if it determines that one or more of the following circumstances exist in respect of a micro-financing institution:

a) the license of the micro-financing institution is revoked as stipulated under sub-article 1(a) of Article 8 of this Proclamation;

b) the micro-financing institution's assets are less than its obligations towards its depositors and creditors;

c) substantial dissipation of assets or earnings due to a violation of any statute or directive or unsafe and unsound practice;

d) the micro-financing institution is in an unsafe and unsound condition to transact business;

e) the micro-financing institution willfully violated any limitations imposed by the National Bank;

f) concealment or refusal to submit the micro-financing institution's books, papers, records or assets for inspection to any inspector or to any lawful agent of the National Bank;

ሰ/ አነስተኛ የፋይናንስ ተቋሙ በመደበኛ የሥራ ሂደት ግዴታዎቹን ወይም የገንዘብ አስቀማጮቹን ጥያቄ ማሟላት አይችልም የሚል ጠንካራ ግምት ከኖረ፤

ሸ/ አነስተኛ የፋይናንስ ተቋሙ ካፒታሉን በሙሉ ወይም የካፒታሉን አብዛኛውን ክፍል የሚያመናምን ኪሳራ የደረሰበት ወይም እንደሚደርስበት የሚገመት ከሆነ፤

ቀ/ አነስተኛ የፋይናንስ ተቋሙ አነስተኛ የፋይናንስ ሥራ ውጪ ከተሰማራ፤

በ/ ከብሔራዊ ባንክ በቅድሚያ በጽሑፍ ፈቃድ ሳያገኝ ከማናቸውም ሌላ አነስተኛ የፋይናንስ ተቋም ወይም ባንክ ጋር የተቀላቀለ ከሆነ፤

ተ/ አነስተኛ የፋይናንስ ተቋሙ፤

/፩/ በብሔራዊ ባንክ የሚጠየቀውን አነስተኛ የካፒታል መጠን የማያሟላና ወደፊትም ካፒታሉን በሚያስፈልገው መጠን ለመጨመር አቅም እንደማይኖረው የሚገመት፣

/፪/ በብሔራዊ ባንክ ሲታዘዝ ካፒታሉን በሚያስፈልገው በቂ መጠን መጨመር ያልቻለ ወይም ብሔራዊ ባንክ በሚወስነው የጊዜ ገደብ ውስጥ ካፒታሉን መልሶ ለመገንባት የሚያስችል ተቀባይነት ያለው ዕቅድ ያላቀረበ፣ ወይም

/፫/ ለብሔራዊ ባንክ ቀርቦ ተቀባይነት ያገኘ ካፒታልን መልሶ የመገንባት ዕቅድ ተግባራዊ ማድረግ ያልቻለ፣

ከሆነ፤

ቸ/ ባለአክሲዮኖች ከብሔራዊ ባንክ በቅድሚያ ፈቃድ በማግኘት ተቋሙን ለማፍረስ የወሰኑ እንደሆነ ወይም ተቋሙ እንደ አንድ ራሱን ችሎ የሚንቀሳቀስ ሕጋዊ ሰው ሆኖ መቀጠል የተሳነው ከሆነ፤

ኀ/ በባለአክሲዮኖች በተላለፈ ውሳኔ ተቋሙ በሞግዚት አስተዳደር ስር እንዲውል የተጠየቀና በብሔራዊ ባንክ የጸደቀ ከሆነ።

g) there is a strong likelihood that the micro-financing institution may be unable to pay its obligations or meet its depositors' demands in the normal course of business;

h) the micro-financing institution has incurred, or is likely to incur, losses that will deplete all or substantial part of its capital;

i) the institution has engaged in activities other than micro-financing business;

j) the institution has merged with another micro-financing institution or a bank without the prior written authorization of the National Bank;

k) the micro-financing institution:

(1) is undercapitalized and has no reasonable prospect of becoming adequately capitailized;

(2) fails to become adequately capitalized when required to do so by the National Bank, or fails to submit a capital restoration plan acceptable to the National Bank within the time prescribed by the National Bank; or

(3) materially fails to implement a capital restoration plan submitted and accepted by the National Bank;

l) shareholders of the institution have decided, subject to approval of the National Bank, to dissolve the institution or the institution has ceased to exist as legally or operationally independent entity;

m) the micro-financing institution, by resolution of its shareholders, and subject to approval of the National Bank, has requested to be put under receivership.

፪/ ብሔራዊ ባንክ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ /፩/ መሠረት ለተሾመ ሞግዚት የሚከፈለውን ክፍያ ይወስናል፡፡

፫/ አነስተኛ የፋይናንስ ተቋም የሞግዚት አስተዳደርና የማፍረስ ሂደት አግባብ ባላቸው የባንክ ሥራ አዋጅ ድንጋጌዎች መሠረት ይከናወናሉ፡፡

## ክፍል አራት
## ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

### ፳. ፈቃድ የተሰጣቸውን አነስተኛ የፋይናንስ ተቋማት ስለማስታወቅ

ብሔራዊ ባንክ በዓመታዊ ሪፖርቱ ውስጥ ፈቃድ የተሰጣቸውን አነስተኛ የፋይናንስ ተቋማት ዝርዝር አትሞ ያወጣል፡፡ እንዲሁም በዚሁ ዝርዝር ላይ የተጨመሩትን ወይም ከዝርዝሩ የተሰረዙትን አነስተኛ የፋይናንስ ተቋማት ሰፊ ስርጭት ባላቸው ጋዜጦች ላይ ወዲያውኑ አሳትሞ ያወጣል፡፡

### ፳፩. አነስተኛ የፋይናንስ ተቋም ወደ ባንክ ወይም ወደ ሌላ የፋይናንስ ተቋምነት ስለሚሸጋገርበት ሁኔታ

፩/ ማናቸውም አነስተኛ የፋይናንስ ተቋም ብሔራዊ ባንክ ያወጣቸውን መስፈርቶች አሟልቶ ጥያቄ ያቀረበ እንደሆነ፣ ባንክ ወይም ሌላ የፋይናንስ ተቋም ሆኖ አግባብ ባለው ሕግ መሠረት እንዲሰራ ብሔራዊ ባንክ እንደገና ፈቃድ ሊሰጠው ይችላል፡፡

፪/ ማናቸውም አነስተኛ የፋይናንስ ተቋም በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ /፩/ መሠረት እንደገና ፈቃድ ከተሰጠው፣ ብሔራዊ ባንክ ተቋሙ አነስተኛ የፋይናንስ ሥራን እንደ አንድ የሥራ ዘርፍ አድርጐ እንዲቀጥል ሊያዘው ይችላል፡፡

### ፳፪. ድጋፍ ስለማግኘት

አነስተኛ የፋይናንስ ተቋማት ለማበደር ወይም ካፒታላቸውን ለመገንባት ከሀገር ውስጥ ወይም ከውጭ ምንጮች ዕርዳታ ሊያገኙ ይችላሉ፡፡

2/ The National Bank shall determine the fee to be paid to a receiver appointed pursuant to sub-article (1) of this Article.

3/ The receivership and liquidation of a micro-financing institution shall proceed in accordance with the relevant provisions of the Banking Business Proclamation.

## PART FOUR
## MISCELLANEOUS PROVISIONS

### 20. Publication

The National Bank shall, in its annual report, publish the list of licensed micro-financing institutions. It shall also publish in newspapers of wide circulation any additions to or cancellation from the said list.

### 21. Transformation of a Micro-Financing Institution to a Bank or other Financial Institution

1/ The National Bank may, upon request, re-license a micro-financing institution that meets the criteria set by the National Bank to operate, in accordance with the relevant law, as a bank or another type of financial institution.

2/ Where a micro-financing institution is re-licensed in accordance with sub-article (1) of this Article, the National Bank may require it to continue providing micro-financing services as part of its operations.

### 22. Assistance

Micro-financing institutions may obtain grant from local or foreign sources for the purpose of on-lending or capitalization.

## ፳፫. ከትርፍ ገቢ ግብር ነፃ ስለመሆን

ማንኛውም አነስተኛ የፋይናንስ ተቋም ከሥራው ያገኘውን ትርፍ፤

፩/ ለባለአክስዮኖቹ ከአከፋፈለ እንደማንኛ ውም የንግድ ተቋም የትርፍ ገቢ ግብር ይከፍላል፤

፪/ በሙሉ ለተቋሙ ሥራ ካዋለው ከትርፍ ገቢ ግብር ነፃ ይሆናል፡፡

## ፳፬ የደንበኞች ማንነት ስለማወቅ

አነስተኛ የፋይናንስ ተቋማት የደንበኞቻቸውን ማንነት በትጋት ተከታትለው የሚያውቁባቸው ንና አጠራጣሪ የሂሳብ እንቅስቃሴዎችን ሪፖርት የሚያደርጉባቸውን መስፈርቶች ብሄራዊ ባንክ በመመሪያ ሊወሰን ይችላል፡፡

## ፳፭. ክ ል ከ ላ

ማንኛውም የውጭ ሀገር ዜጋ ወይም ሙሉ በሙሉም ሆነ በከፊል በውጭ ሀገር ዜጎች ባለቤትነት የተያዘ ድርጅት አነስተኛ የፋይናንስ ተቋም ለማቋቋም ወይም ቅርንጫፍ ለመክፈት ወይም የውጭ ሀገር አነስተኛ የፋይናንስ ተቋም ተቀጽላ በመሆን በኢትዮጵያ ውስጥ ሥራ ለመሥራት ወይም በኢትዮጵያ ውስጥ በተቋቋመ አነስተኛ የፋይናንስ ተቋም የአክሲዮን ባለቤት ለመሆን አይፈቀድለትም፡፡

## ፳፮. ቅ ጣ ት

፩/ ማንኛውም አነስተኛ የፋይናንስ ተቋም ዳይሬክተር፣ የሥራ ኃላፊ ወይም ሠራተኛ፣

ሀ/ ማንኛውም ኦዲተር በዚህ አዋጅ ድንጋጌዎች መሠረት የተጣሉበትን ግዴታዎች መፈጸም እንዳይችል ወይም በብሔራዊ ባንክ ሥልጣን የተሰጠው ተቆጣጣሪ በአነስተኛ የፋይናንስ ተቋሙ ላይ ተገቢውን ቁጥጥር እንዳያካሂድ እንቅፋት ከሆነ፣ ወይም

ለ/ ለማታለል በማሰብ የሐሰት ወይም አሳሳች መግለጫ የሰጠ ወይም በአነስተኛ የፋይናንስ ተቋሙ መዝገብ፣ ሂሣብ፣ ሪፖርት ወይም መግለጫ ውስጥ የመዘገበ እንደሆነ ወይም መመዝገብ የነበረበትን መግለጫ ወይም መረጃ ሳይመዘግብ የቀረ እንደሆነ፣

ከብር ፶ሺ እስከ ብር ፩፻ሺ በሚደርስ መቀጫ እና ከ፲ እስከ ፲፭ ዓመት በሚደርስ ጽኑ እሥራት ይቀጣል፡፡

## 23. Exemption from Profit Tax

Any micro-financing institution that makes profit from its business and;

1/ distributes to shareholders shall pay profit tax as any business entity,

2/ fully ploughs back shall not pay profit tas.

## 24. Know-Your-Customer Standards

The National Bank may issue directive prescribing standards on micro-financing institutions' due diligence in knowing their customers and reporting of suspicious transactions.

## 25. Prohibitions

Any foreign national or organization fully or partially owned by foreign nationals may not be allowed to establish a micro-financing institution, open branches or subsidiaries of a foreign micro-financing institution in Ethiopia or to acquire the shares of an Ethiopian micro-financing institution.

## 25. Penalties

1/ Any director, officer or employee of a micro-financing institution who;

a) obstructs the proper performance by an auditor of his duties in accordance with the provisions of this Proclamation or inspection of a micro-financing institution by an inspector duly authorized by the National Bank; or

b) with intent to deceive, makes any false or misleading statement or entry, or omits any statement or entry that should be made in any book, account, report or statement of micro-financing institution;

shall be punished with a fine from Birr 500,000 to Birr 100,000 and with rigorous imprisonment from 10 to 15 years.

፪/ የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ /፩/ ድንጋጌ እንደተጠበቀ ሆኖ ማንኛውም ሰው የዚህን አዋጅ ድንጋጌዎች ወይም ይህን አዋጅ ለማስፈጸም የወጡ ደንቦችን ወይም መመሪያዎችን የተላለፈ ወይም አፈፃጸማቸውን ያሰናከለ እንደሆነ እስከ ብር ፲ሺ በሚደርስ መቀጫና እስከ ሦስት ዓመት በሚደርስ እሥራት ይቀጣል፡፡

## ፳፯ <u>ደንብና መመሪያ የማውጣት ሥልጣን</u>

፩/ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ይህን አዋጅ ለማስፈፀም የሚያስፈልጉ ደንቦችን ሊያወጣ ይችላል፡፡

፪/ ብሔራዊ ባንክ ይህን አዋጅና በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ /፩/ መሠረት የወጡ ደንቦችን ለማስፈጸም የሚያስፈልጉ መመሪያዎችን ለማውጣት ይችላል፡፡

## ፳፰. <u>ተፈፃሚነት ስለሚኖራቸው ሌሎች ሕጎች</u>

፩/ የባንክ ሥራ ሕጎች በዚህ አዋጅ ያልተሸፈኑ ጉዳዮችን በሚመለከት በአነስተኛ የፋይናንስ ሥራ ላይ እንደአግባቡ ተፈፃሚ ይሆናሉ፡፡

፪/ በባንክ በመያዣ ስለተያዘ ንብረት የወጣው አዋጅ ቁጥር ፺፯/፲፱፻፺፰ እና ስለንግድ ተቋም የዋስትና መያዣ የወጣው አዋጅ ቁጥር ፺፰/፲፱፻፺፰ በአነስተኛ የፋይናንስ ተቋም በመያዣ የተያዘ ንብረት ላይ እንደአግባቡ ተፈፃሚ ይሆናሉ፡፡

## ፳፱. <u>የተሻሩና ተፈጻሚነት ስለማይኖራቸው ሕጎች</u>

፩/ ለአነስተኛ ብድር አቅራቢ የገንዘብ ድርጅቶች ፈቃድ ስለመስጠትና ሥራቸውን ስለመቆጣጠር የወጣው አዋጅ ቁጥር ፵/፲፱፻፹፰ በዚህ አዋጅ ተሽሯል፡፡

፪/ ከዚህ አዋጅ ጋር የሚቃረን ማናቸውም ሕግ፣ ደንብ፣ መመሪያ ወይም የአሠራር ልምድ በዚህ አዋጅ በተደነገጉ ጉዳዮች ላይ ተፈጻሚ አይሆንም፡፡



2/ Without prejudice to sub-article (1) of this Article, any person who contravenes or obstructs the provisions of this Proclamation or regulations or directives issued to implement this Proclamation shall be punished with a fine up to Birr 10,000 and with an imprisonment up to three years.

## 27. <u>Issuance of Regulations and Directives</u>

1/ The Council of Ministers may issue regulations necessary for the implementation of this Proclamation.

2/ The National Bank may issue directives necessary for the implementation of this Proclamation and the regulations issued in accordance with sub-article (1) of this Article.

## 28. <u>Applicability of other Laws</u>

1/ Banking business laws shall, mutatis mutandis, be applicable to micro financing business with respect to matters not covered by this Proclamation.

2/ Property Mortgaged or Pledged with Banks Proclamation No. 97/1998 and Business Mortgage Proclamation No. 98/1998 shall, mutatis mutandis, be applicable with respect to property mortgaged or pledged with micro-financing institutions.

## 29. <u>Repealed and Inapplicable Laws</u>

1/ The Licensing and Supervision of the Business of Micro-financing Institutions Proclamation No. 40/1996 is hereby repealed.

2/ No law, regulations, directives or practice may, in so far as it is inconsistent with the provisions of this Proclamation, be applicable with respect to maters provided for by this Proclamation.

## ፴. አዋጁ የሚፀናበት ጊዜ

ይህ አዋጅ በፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል።

**አዲስ አበባ ግንቦት ፬ ቀን ፪ሺ፩ ዓ.ም**

**ግርማ ወልደጊዮርጊስ**

**የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ፕሬዚዳንት**

## 30. Effective Date

This Proclamation shall enter into force up on the date of publication in the Federal Negarit Gazeta.

**Done at Addis Ababa, this 12th day of May , 2009**

**GIRMA WOLDEGIORGIS**

**PRESIDENT OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA**